# ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው
## *አርዮሳውያን ነበሩ ወይስ ሥላሴያውያን?*

*የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከውልደቷ ጀምሮ በዚህ ምድር በኖረችባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ ህልውናዋን የሚፈታተኑ በርካታ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች ገጥመዋታል። በአንጻራዊነት ሲታይ፣ አንዳንዶቹ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ያገኙ ቢሆንም፣ አንዳንዶቹ ግን በየትኛውም የታሪክ ዘመን ሳያጨቃጭቁ ያለፉበት ጊዜ የለም ማለት ይቻላል። ከእነዚህ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች ውስጥ ትምህርተ ሥላሴ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል ቢባል እብለትም ሆነ ግነት የለበትም[1]። ይህ የትምህርት ጊዜ ራሱ ይህ እውነት ለመሆኑ አንድ ምልክት ነው።*

*የትምህርተ ሥላሴ ቀዳማይ አመንጪ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም፣ በሐዋርያት እግር ሥር የተማሩት ሐዋርያዊ አባቶች እንዲሁም በሁለተኛውና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት ቀደምትና ደኅርት[2] የቤተ ክርስቲያን አበው፣ ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ ምን አሉ የሚለው ጉዳይ ለሥላሴ አማንያንም ሆነ ትምህርተ ሥላሴን ለማይቀበሉ ሰዎች መሠረታዊ ጉዳይ እየሆነ መጥቶአል። በዚህ ረገድ የሚከሠተውን የታሪክ ግርምቢጥ፣ ተአማኒ የሆኑ የታሪክ ምስክሮችን በእማኝነት በማቆም፣ እርስ በርሳቸው የተምታቱና የተውገረገሩ አመለካከቶችን ማረም እውነት ወዳድ ከሆኑ ሰዎች በተለይም ከክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የሚጠበቅ ጉዳይ ሆኖአል። "ብርሃን ናችሁ"፣ "ጨው ናችሁ" የሚለው የጌታ ትምህርት፣ ሥነ ምግባርን ብቻ ሳይሆን እኩይም (እንደ ጌታ ትምህርት አልጫም) ሆኑ ሠናይ (እንደ ጌታ ትምህርት ጨለማ) ሥነ ምግባሮች የሚፈልቁባቸውን የአስተሳሰብ ምንጮች በማጥራት ረገድ፣ በጌታ ደቀ መዛሙርት ላይ ትልቅ ኀላፊነት የሚጥል ነው።*

*ትምህርተ ሥላሴን ከአርዮስ አስተምህሮ በመከላከል ረገድ ትልቅ ቦታ ከነበራቸው የቤተ ክርስቲያን አበው መካከል አትናቴዎስ ዘእስክንድርያ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ቢሆንም፣ ርእሰ ጉዳዩን በጠለለና በዳበረ መልኩ ያቀረቡት ቀጰዶቃውያን አበው[3] ናቸው።*

*በርካቶች በተለይም የይሖዋ ምስክሮችና የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን፣ ትምህርተ ሥላሴ ከቃለ እግዚአብሔር የተቀዳ ሳይሆን፣ ከጉባኤ ኒቂያ በኋላ[4] የመጣ ባዕድ*

---

[1] ተስፋዬ ሮበሌ፣ *የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ አዲስ አበባ፣ 1998 ዓ.ም)፣ 17-21።

[2] ደኅርት ማለት ኋለኛ፣ የኋላ፣ ታናሽ፣ ተከታይ ወዘተ ማለት ነው። ሐዋርያዊ አባቶች (Apostolic Fathers) እንዲሁም ቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች (Second-Century Fathers) ደኅርት የቤተ ክርስቲያን አባቶች (Third-Century Fathers)።

[3] ቀጰዶቃውያን አበው (Cappadocian Fathers) የሚባሉት፣ የቂሳርያው ትልቁ አባት ባስልዮስ (Basil The Great)፣ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ (Gregory of Nazianzus) እንዲሁም ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (Gregory Nyssa) ናቸው። በዚህ መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስም የምንጠቅሰው፣ የጥንት ብራና መጻሕፍት በሚጠቀሙበት መንገድ ነው። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዐውዳዊ ነገረ መለኮት (contextualize theology) የሚለውን ጉዳይ ትኩረት የሚሰጡበት እስከ ሆነ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስያሜ በተመለከተ ትልቅ ትኩረት ሊሰጡበት የሚገባ ይመስለኛል።

[4] ጉባኤ ኒቂያ በጎርጎሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 325 ዓ.ም በጁሊያን የዘመን አቈጣጠር 318 ዓ.ም የተካሄደ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው።

አስተምህሮ ነው የሚል አመለካከት አላቸው። ጉባኤ ኒቂያ በሮማው ቄሳር ቈስጠንጢኖስ[5] የተጠራበት ዋነኛ ምክንያት፣ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበረው አርዮስ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር በሁሉ ነገር ትክክል አይደለም" የሚለው አቋም በወቅቱ የነበሩትን የነገረ መለኮት ምሁራንንና የቤተ ክርስቲያን አባቶችን በአያሌው በማሳሰቡ ነበር። በምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን የተነሣው ይህ የነገረ መለኮት ውዝግብ በምዕራብም ሆነ በምሥራቅ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ለችግሩ አፋጣኝና ሁነኛ እልባት ታፈላልግ ዘንድ ግድ አለ። በ325 ዓ.ም ይህ ጉባኤ ከመካሄዱ በፊት ሃምሳ ዘጠኝ ሊቃነ ጳጳሳት በአንጾኪያ በመሰብሰብ አርዮስን ሊያወግዙ ዕቅድ አውጥተው ሳለ፣ በግዛተ ዐፄው ውስጥ የተፈጠረው ይህ ውዝግብ እጅግ ያሳሰበው ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በወርኀ ሰኔ 325 ዓ.ም ላይ፣ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት የሚሆኑ ሊቃነ ጳጳሳትና የነገረ መለኮት ምሁራንን በኒቂያ በመሰብሰብ በርእሰ ጉዳዩ ላይ እንዲመክር አደረገ። አንዳንድ መረጃዎች ከምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤውን የተካፈሉ የኮርዶቫው ኦስዮስ (Ossius of Cordova) እና ሌሎች ሁለት በስም የማይታወቁ የቤተ ክርስቲያን መጋቢያን ብቻ ነበሩ ባይ ናቸው።

ይህ አርዮስ ያስነሣውና ጉባኤ ኒቂያ የመከረበት የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳይ ከመካሄዱ በፊት፣ የአብንና የወልድን ግንኙነት አስመልክቶ የተነሣ ሌላ የነገረ መለኮት ፍጭት ነበር። በነገረ መለኮቱ ዓለም፣ ሞዳልስቲክ ሞናርኪያሊዝምና ዳይናሚክ ሞናርኪያሊዝም (አዶብሽኒዝም) በመባል ለሚታወቁት አስተምህሮዎች ቀዳማይ ጠንሳሽ ነው የሚባለው የቤዛንታዪኑ ቈዳ ነጋዴ ቴዎዶቱስ (Theodotus)፣ በ190 ዓ.ም ይህን ትምህርት ወደ ምድረ ሮም እንዳስገባ የነገረ መለኮት ምሁር እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ዐቃቤ እምነት የነበረው ሰማዕቱ ሂፖሊተስ[6] እንዲሁም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሓፊ አውሳቢዮስ ዘቂሳርያ ገልጸዋል[7]። በወቅቱ የሮም ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የነበረው ቪክቶር ቴዎዶቱስን በአስተምህሮው ምክንያት በተግሣጸ ቤተ ክርስቲያን፣ ተወግዞ ተባሮ ነበር። ነገር ግን የአዶብሽኒዝም አስተምህሮ ቀንደኛ መምህር በመሆን ታሪክ በስፋት የሚያውቀው የሳሞሳታው ጳውሎስ ነው (Paul of Samosata)። የሞደልስቲክ ሞናርኪያሊዝም ትምህርት ጠንሳሽ ነው ትብሎ የሚታሰበው የሰሚርናው ኒዎጡስ (Noetus of Smyrna 190 ዓ.ም) ቢሆንም፣ አስተምህሮውን በማስፋፋት የአስተምህሮው አባት ተደርጎ በታሪክ የሚታወቀው የሊቢያው ቄስ ሳባልዮስ ነው። ግለሰቡ አስተምህሮውን በማስፋፋትም ሆነ፣ ትምህርቱን በተጠናከረ መልኩ በማስተማር በስፋት እየታወቀ በመሄዱ ምክንያት፣ የዚህ አስተምህሮ ደጋፊዎች በሙሉ ሰባልዮሳውያን እየተባሉ ይጠሩ ዘንድ ግድ ሆኖአል[8]። ቄስ ተክለ ማርያም ገዛኸኝ እርሳቸው በበላይነት የሚመሩት ቤተ ክርስቲያን የሰባልዮስን አስተምህሮ እንደምትከተል በይፋ አስታውቀዋል[9]። ቄስ ተክለ ማርያም ይህን ይበሉ እንጂ፣ የኢትዮጵያ የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ከሰባልዮስ አስተምህሮ ጋር አንዳችም መጋጠም የለውም—ሊመስል ይችል ይሆናል። ከሰባልዮሳውያን አስተምህሮ በብዙ መልኩ የተለየና የደደረ ኑፋቄ ነው—ስሕተትን ማበላለጥ አስቸጋሪ ቢሆንም።

[5] በወቅቱ የአገረ ሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረ።

[6] (Hippolytus ✞235) Hippolytus, "The Heresy of Theodotus," in *The Refutation of All Heresies,* 7.23, in *The Ante-Nicene Fathers,* vol. 1 (New York: Charles Scribner's Sons, 1899).

[7] (Eusebius of Caesarea 260-339 ዓ.ም) Eusebius, *History of the Church,* 7.27, in *Eusebius, The History of the Church: A New Translation with Commentary,* trans. Paul Maier (Grand Rapids: Kregel, 1999),

[8] ስለ ሰባልዮሳውያን አስተምህሮና ታሪክ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ሰባልዮሳውያኑ-የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፣* የሚለውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

[9] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፣ *ኢየሱስን ማን ይሉታል?* (1978 ዓ.ም) ገጽ 4።

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን "ውጉዝ ከመአርዮስ ወውጉዝ ከመሰባልዮስ" ትበል እንጂ፣ ዘመነኞቹ ሰባልዮሳውያንም ሆኑ አርዮሳውያን፣ የሥላሴ አስተምህሮ ጥንስሱም ሆነ ውቅሩ ጉባኤ ኒቂያ ነው፣ ከዚያ በፊት የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አበው ሥላሴያዊ አመለካከትም ሆነ አስተምህሮ አልነበራቸውም የሚል ሙግት በማራመድ ላይ ናቸው።

የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምን ዐይነት አስተምህሮ ነበራት የሚለው ጉዳይ መልስ የሚያገኘው፣ (1) ቃለ እግዚአብሔር በርእሰ ጉዳዩ ላይ ምን ትምህርት አለው፣ (2) ታሪክ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እምነቷ፣ አስተምህሮዋና ሥርዐተ አምልኮዋ ምን ይመስል እንደ ነበረ ይገልጻል በሚሉት ሁለት አዕማድ ማገናዘቢያዎች አማካይነት ብቻ ነው። ውዝግቡን በበሰለና ምሁራዊ አካሄድ በተከተለ መንገድ ለመፍታት ብቸኛ ጐዳና ይኸው ከሆነ፣ ይህን አካሄድ መከተል የግድ ይሆናል፤ እኛም የታሪክ ስሕተትን በታሪክ ለማረቅ ታሪካዊ ሰነዶችን በማቅረብ ውይይታችንን ለማካሄድ ትልቅ ሙከራ ለማድረግ እንሞክራለን።

ቅድሚያ ሰጥተን የምንነጋገረው የአርዮሳውያኑን የይሖዋ ምስክሮች የሙግት ነጥብ አወቃቀር ላይ ሲሆን በቀጣይነት ደግሞ የሰባልዮሳውያኑን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሙግት በወፍ በረርም ቢሆን ለማቃኘት እንሞክራለን።

# በሥላሴ ማመን አይገባህምን?

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት፣ "የይሖዋ ምስክሮች" ብሎ ለሰየማቸው የድርጅቱ አባላት፣ በኅብረ ቀለማት ባሸበረቁ ጽሑፎቹ ስለ ራሱ በተደጋጋሚነት የሚነግራቸው የሚከተሉትን ትምህርቶች ነው[10]:—

- የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያስተምር አንድ የሃይማኖት ድርጅት ብቻ እንዳለ[11]፣ ይህም ድርጅት የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር እንደ ሆነ[12]፣
- የድርጅቱ አባላት ለዚህ ብቸኛ ድርጅት ብቻ መገዛት እንዲሁም አስተምህሮውን እንደ አምላክ ድምፅ መታዘዝ እንዳለባቸው[13]፣
- እንዲያውም፣ "እግዚአብሔር ከሚጠቀምበት ከዚህ ድልድይ [የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር] ጋር ግንኙነት ከሌለን፣ ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብም በሕይወት ጐዳና እርምጃ ልናሳይ እንችልም"[14]።
- ቅዱሳት መጻሕፍትን የማብራራትና የማስተማር ሥልጣን ያለው ብቸኛ የዓለማችን ድርጅት እንደ ሆነ[15]፣ የይሖዋ ምስክሮች የድርጅቱን አስተምህሮ ለሚቀርጸውና ልባምና

---

[10] የዚህ ክፍል ሐሳብ የተወሰደው ከሚከተለው መጽሐፍ ነው:— ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* (ራዕይ አሳተሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ 1991 ዓ.ም), 50-60። ስለ ይሖዋ ምስክሮችና ስለድርጅታቸው ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ይህን መጽሐፍ ይመለከቷል።

[11] *በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ* (1991), 191-195፤ *ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር* (1994), 280-284 ይመለከቷል።

[12] *The Watchtower,* 15 June 1957, 274።

[13] ዝኒ ከማሁ።

[14] *The Watchtower,* 1 December 1981, 27 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

[1515] *The Watchtower,* 1 May 1957, 274. *The Watchtower,* 15 January 1983, 22 *The Watchtower,* 15 September 1911, 2885.

ታማኝ ባርያ በመባል ለሚታወቀው ድርጅት ለጥ ሰጥ ብለው መገዛት እንደሚጠበቅባቸው[16]::

- በአንጻሩ ደግሞ ሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ በዲያቢሎስ መንፈስ የሚመሩ ሰይጣናዊ ድርጅቶች መሆናቸውን[17]፣
- የእነዚህ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ጽሑፍ ማንበብ በተለይ ደግሞ ድርጅቱን ለቀው ከወጡ ሰዎች ጋር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ውይይት ማካሄድ እንዲሁም ጽሑፎቻቸውን ማንበብ በጥብቅ የተከለከለ ነው[18]:: በደርጅቱ አስተምህሮ ላይ ሒስ የሚሰነዝሩ ሰዎች ሁሉ "ተቃዋሚዎች" ተብለው የሚፈረጁ ስለሆነ የእነዚህን ግለሰቦች ጽሑፍ ማንበብ "መንፈሳዊ በሆነ ገበታ ላይ፣ መንፈሳዊ የዝሙት ሥዕል መመልከት ነው" የሚል ጽኑ እምነት አለው::

መጽሐፍ ቅዱስ የሃይማኖት ሰዎች ሁሉን መመርመር መልካሙን ደግሞ የመያዝ ኀላፊነት አለባቸው:: በቤሪያ ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች፣ "ልበ ሰፊዎች" የተባሉበት ሁነኛ ምክንያት፣ የሐዋርያውን የጳውሎስን ጽሑፎችና ትምህርቶች በትጋት ይመረምሩ ስለነበር እንደ ሆነ ልብ ይሏል::

"አትመርምሩኝ"፣ "እኔ ብቻዬን የአምላክ ድርጅት ነኝ"፣ "ሌሎች ግለሰቦችም ሆኑ የሃይማኖት ድርጅቶች ሰይጣናዊ ናቸው"፣ ወዘተ እያለ የሚያስተምረው ትምህርት እውነተኛነቱ እንዴት ሊመሳከር ይችላል? "አትመርምሩ" "ዝም ብላችሁ ተቀበሉ" በተባለበት ሁኔታ? አላንዳች ማመሳከሪያ እንዲሁም ማመሳከሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን መሠረቶች ሁሉ በመደምሰስ ስለራስ ይህ ዐይነቱን ምስክርነት መስጠት ተገቢ ነውን?

አስደናቂው እውነት ግን ድርጅቱ ስለራሱ ይህን መሰሉን ምስክርነት እየሰጠ አባላቱን የሚያስተምረው ትምህርት፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት እጅግ የራቀ ስለ መሆኑ እጅግ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል[19]::

ይህ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት፣ "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" በሚል ርእስ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1989 ዓ.ም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባዘጋጀውና በ1993 ዓ.ም በአማርኛ ቋንቋ ባስተረጐመው መጽሐፍ:— (1) ትምህርተ ሥላሴ ከአረማውያን መድብለ አማልክት አስተሳሰብ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስን ተገን በማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ የገባ ባዕድ ትምህርት እንደ ሆነ፣ (2) አስተምህሮው በቅዱሳት መጻሕፍት አንዳችም ድጋፍ ሳይኖረው እንዲያው በዐዋጅና በልማድ የሚታመን መሠረተ እምነት መሆኑን ሰዎች ይረዱ ዘንድ፣ "የይሖዋ አምላክ እንደ ራሴ" በመሆን ሰዎችን "ያነቃል"፣ (3) ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አበው በትምህርተ ሥላሴ እንደማያምኑ፣ (4) እንዲያውም እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አርዮሳዊ እምነትና አስተምህሮ እንደ "ነበራቸው" (5) የሥላሴ አስተምህሮ የሥነ አመክንዮ ሊቆም የማይችል የተወላከፈ እንዲያውም እርስ በርሱ የሚጣረስ አስተምህሮ

---

[16] *The Watchtower,* 1 May 1964, 277.

[17] *የይሖዋን ፈቃድ ለማድረግ የተደራጀ ሕዝብ* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 2005).

[18] *ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር* (1994), 33-36 ይመለከቷል::

[19] ስለ ይሖዋ ምስክሮችና ስለድርጅታቸው ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የሚከተለውን መጽሐፍ ይመለከቷል:— ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* (ራዕይ አሳተሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ 1991 ዓ.ም)::

እንደ ሆነ በኅበረ ቀለማት ባሸበረቁና እጅግ ውብ በሆኑ ፎቶ ግራፍና ሥዕሎች በመታገዝ ተንተናውንና ሙግቱን ያቀርባል[20]።

ድርጅቱ ይህን ድምዳሜ ይደግፍለት ዘንድ እንዲሁም አርዮሳዊ አስተምህሮው ለማጽናት፣ የተከተለባቸው የሙግት አወቃቀሮችና ከሙግት ነጥቦቹ በመንደርደር የደረሰባቸው ድምዳሜዎች አራት መሠራዊና ጉልሕ ችግሮች ይታይባቸዋል። ችግሮቹ እነሆ:—

## I. ዐውዳቸውን ያልጠበቁና የጸሓፍያኑን ሐሳብ በትክክል የማይወክሉ መረጃዎች

የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት በዋቢነት ያቀረባቸው መረጃዎች፣ ዐውዱን ባልጠበቀና የጸሓፍያኑን ሐሳብ በትክክል በማይወክል መንገድ ማብራሪያ የቀረበላቸው ከመሆናቸውም በላይ፣ አንባብያን ከጸሓፊው ሐሳብ ጋር ፈጽም ወደሚቃረኑ ድምዳሜዎች ላይ እንዲደርሱ ተደርጓል። ይህ ምን ያህል እውነት እንደ ሆነ በዚህ ጽሑፍ በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን የምንመለከተው ጉዳይ ይሆናል[21]። ቀሎም ነገሩን ያዋዛልን ዘንድ አስረጅ እንጠቀም።

"የሥላሴ አስተምህሮ በየዘመናቱ እየጠራ መጣ" የሚለውን የምሁራን ንግግር፣ ድርጅቱ ለመሠረተ እምነቱ ፍጆታ የሚጠቀምበት አስተምህሮው በቃለ እግዚአብሔርም ሆነ ከኒቂያ ጉባኤ በፊት በነበሩት ዘመናት አይታወቅም ነበር የሚለውን ሐሳቡን ለማጠናከር ነው። ሊቃውንቱ "ጠራ" ወይም "ጐለበተ" የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት በወቅቱ አስተምህሮውን አስመልክቶ የተነሣውን መደፍረስ እንዲሁም ከጊዜ በኋላ በተነሡት የነገረ መለኮት ምሁራን አስተምህሮውን በጥሩ ሁኔታ የመተንተናቸውን ጉዳይ ለማሳየት ነው። "ጠራ" ወይም "ጐለበተ" ማለት አዲስ ግኝት ተገኘ ማለት አይደለም[22]።

---

[20] እኛ ዛሬ በድርጅቱ ጽሑፍ ላይ ይህን ሒስ ማቅረብ የቻልነው፣ የድርጅቱን ጹሑፎች በጥሞና በማንበብ እስከ ሆነ ድረስ፣ የድርጅቱ አባላትም፣ "የተቃዋሚዎች ስም ማጥፋት ነው" በሚል ሙግታችንን በደፈናው ሊያጣጥሉ አይገባም። "ስም ማጥፋት" መሆኑን እንኳ በትክክል መረዳት የሚቻለው፣ መረጃውን ማንበብ ሲቻል ብቻ ነው። "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" በሚለው በድርጅቱ መጽሐፍ ላይ በውል እንደታየው፣ "ታማኝና ልባም ባሮች" በመባል የሚታወቁት የድርጅቱ ጸሓፍያን፣ ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ ወደዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሱት፣ በርካታ መጻሕፍትን አንብበው እንደ ሆነ በጽሑፎቻቸው ላይ እስከ ጠቀሱ ድረስ፣ የድርጅቱ አባላት፣ "የተቃዋሚዎችን ጽሑፍ አታንብቡ" መባላቸው እርስ በርሱ የሚጣረስ አልያም፣ "እኔ ብቻ አውቅልሃለው" አልያም "አንተ ለራስህ አትበቃም" እንደ ማለት ይሆናል።

[21] የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በሥላሴ ማመን ይገባሃልን በሚል ርእስ ያዘጋጀው መጽሐፍ መረጃዎችን እንዴት አድርጎ እንደሚያጠምም፣ ቈርጦ እንደሚቀጥል በአጠቃላይ መረጃዎችን በማጠናበር አንባብያኑንም ሆነ የድርጅቱን አባላት ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ እንደሚደርስ ከሚከተለው ድረ ገጽ ላይ በግልጥ መመልከት ይቻላል <http://www.bible.ca/trinity/trinity-jw-deceptions>። ሰዎች ምናልባትም የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ይህን ድረ ገጽ ለማየት ፈቃደኛ ቢሆኑ (ፈቃደኛ እንዳይሆኑ ትልቅ የሆነ ክልከላ አለባቸው ቢሆንም)፣ የአምላክ ብቸኛ ወኪል ነው በሚሉት ድርጅታቸው አረማዊ ትምህርት ነው ያለውን አስተምህሮ በእልልታና በሆታ እንደሚቀበሉት ጥርጥር የለውም። ይህን ድረ ገጽ እንዲመለከቱ ለይሖዋ ምስክር ወዳጆችዎም እንዲያሳዩ በማክበር እንጠ ይቅዎታለን።

[22] "አዲስ" አላልንም እንጂ "አዲስ" ብንል እንኳ፣ "አዲስ" የሆነው ለእኛ ነው። ነገር ግን "አዲስ" የተባለው ነገር ድሮም የነበረ እውነት ነው። ሰዎች እውነትን ያገኛሉ እንጂ እውነትን አይፈጥሩም። ወርኀ የካቲት 2000 ዓ.ም ተፈጠረ/ተወለደ የሚባል እውነት የለም። ተገኘ የሚባል እንጂ። ይህም እውነት በየትኛውም

(1) ከሰነዶቹ በቀጥታ ወስደናቸዋል ያሏቸው መረጃዎች የድርጅቱን አስተምህሮ ብቻ በሚደግፉ መልክ እንዲቀርቡ በማሰብ ድርጅቱ ሦስት ነጥቦችን [ellipses (...)] በመጠቀም ጸሓፍያኑ ለማለት ከፈለጉት ውጪ እንዲያውም ተቃራኒውን ድምዳሜ አንባብያን እንዲረዱ አድርጓል:: ለምሳሌ:—

> "የየል ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ኢ ዋሽበርን ሆኘኪንስ እንዲህ ሲሉ አረጋግጠዋል:— 'በግልጽ እንደሚታየው ኢየሱስና ጳውሎስ ስለ ሥላሴ መሠረተ ትምህርት የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤. . . ስለዚህም መሠረተ ትምህርት የተናገሩት ምንም ነገር የለም'—ኦሪጅን ኤንድ ኢቮሉሽን ኦቭ ሪሊጅን (የሃይማኖት አመጣጥና ዕድገት)" (በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ገጽ 6 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

የሚገርመው ሆፕኪንስ ይህን ከማለታቸው ከፍ ብሎ በሚገኘው ዐረፍተ ነገር ላይ የሚከተለውን ብለዋል:—
"የሥላሴ ጅማሬ በዮሐንስ ወንጌል ላይ ቀድሞውኑ ይገኛል"[23]

ነገር ግን የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጸሓፊው፣ የሥላሴ ትምህርት ለኢየሱስና ለጳውሎስ በዕድ ነው የሚለውን ቢጠቅሱም፣ *"የሥላሴ ትምህርት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ይገኛል"* ሲሉ አከታትለው የጻፉትን ጽሑፍ ገንጥሎ ማስቀረቱ፣ ድርጅቱ የጸሓፊውን ሐሳብ በትክክል እንዳናውቅ እንዲያውም ከጽሑፋቸው የተዛባ ትምህርት እንድናገኝ አድርጓል::

> "ኢ ደብልዩ ሆፕኪንስ ኦሪጅን አንድ ኤቮሉሽን ኦቭ ሪሊጅን (የሃይማኖት ምንጭና ዕድገት) የተባለው መጽሐፍ እንዲህ በማለት መልስ ይሰጣሉ:— 'በመጨረሻ የሥላሴ ትርጉም ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው በአብዛኘው የቤተ ክርስቲያን ፖለቲካ ውጤት ነው'" (በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ገጽ 9 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

ብለዋል ይበል እንጂ ጸሓፊው ከዚህ ቀጥሎ በሚገኘው ዐረፍተ ነገር ላይ:—

> "ቤተ ክርስቲያን...ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያለ አምላክ ነው የሚል የመጀመሪያና ቀላል የሆነ እምነት ነበራት"[24]::

ማለታቸውን ግን አልጠቀሰም::

አስገራሚ የሆነው ሌላው ቊም ነገር እኝህ የታሪክ ምሁር:—

> "የውሃ ጥምቀት፣ ጾም፣ የማንጻት ሥርዐት፣ የድንግል መፀነስ፣ ያለመሞት ተስፋና ትንሣኤ ሙታን፣ ተኣምራዊ የሆነ እርግማን፣ ውሃ ወደ ወይን ጠጅ ተቀይሯል የሚሉት ጉዳዮች ከቅድመ ክርስትና በፊት የነበሩ"ና ከአረማውያን በተለይም ከቡድሂዝም መሠረተ እምነት የተወሰዱ ናቸው[25]::

---

ቦታና ጊዜ አንዲሁም ሁኔታ ውስጥ እውነት ነው:: እውነት እንደማያረጀው ሁሉ፣ እውነት አይፈጠርም፤ አይለወጥምም:: በአንድ ጊዜ እውነት የሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ እውነት ነው::

[23] "The beginning of the doctrine of the Trinity appears already in John " *(c. 100). "To Jesus and Paul the doctrine of the trinity was apparently unknown; . . . they say nothing about it."* (*Origin and Evolution of Religion,* E. W. Hopkins, p 336)

[24] "*The final orthodox definition of the trinity was largely a matter of church politics.* ... The church ... also believed with the first simple Christians that Jesus Christ was God on earth." (Origin and Evolution of Religion, E. W. Hopkins, p339, all quoted within the same paragraph).

[25] *Origin and Evolution of Religion,* E. W. Hopkins, Ch 20, *The Christian Trinity. History of Religions,* 1918, E. Washburn Hopkins, Professor of Sanskrit and comparative Philology, p 552,556.

የሚል አስተምህሮ አላቸው:: እኝህ ሰው በስፋት የሚታወቁት በክርስትና መሠረተ እምነት ላይ በሚሰነዝሩት ሒስ በሆነበት ሁኔታ፣ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ራሱ የሚያምንባቸው መሠረተ እምነቶች ራሳቸው እንኳ ከአረማውያን መድብለ አማልክት የተቀዱ ናቸው የሚልን ምሁር እማኝነት፣ የሥላሴ እምነት ከአረማውያን በድብለ አማልክት የተቀዳ ነው ለሚለው ትምህርቱ ማስደገፊያ አድርጎ ሊያቀርባቸው እንዴት ወደደ?

## II. በእግዚአብሔርና በክርስትና ላይ ሐሰታዊ ምልከታ ያላቸውን ጸሐፍያን በእማኝነት መጥቀስ

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት፣ በዚህ መጽሐፉ መጀመሪያ ላይ፣ "ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ የሥላሴ እምነት ደጋፊዎች የነበሩ ሰዎች በዚህ እምነት ላይ የሚነግሡን ክርክር አፋፍመዋል" (ገጽ 3) በማለት በዚህ መለስተኛ መጽሐፉ ውስጥ ድርጅቱ ወደ 32 የሚደርሱ ምንጮችን የጠቀሰ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ወደ 67 ከመቶ የሚሆኑ ምንጮች የተወሰዱት፣ የሥላሴን አስተምህሮ ከማይቀበሉ የሃይማኖት ክፍሎች ይኸውም:— (1) አርዮሳዊ አመለካከት ካላቸው መምህራን[26]፣ (2) የእስልምና ሃይማኖት ጸሓፍያን፣ (3) የይሁዲ እምነት ሊቃውንት እንዲሁም (4) የተባበሩት ጴንጤቈስጣውያን ጸሓፍያን ይገኙበታል[27]:: (5) ከዚህ በተጨማሪ ድርጅቱ በዚህ መጽሐፉ ላይ በእማኝነት የተጠቀሳቸው ግለሰቦች በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በአልሆተ እግዚአብሔር የማያምኑ ጸሓፍያን ሲሆኑ፣ የግለሰቦቹ ድርሰት ቀዳማይ ዐላማም ክርስቶስንና የክርስትናን መሠረተ እምነቶች መተቸት ነው::

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በመረጃነት ከተጠቀመባቸው ጸሓፍት መካከል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የአንዳንድ ግለሰቦችን የእምነት አቋም ሳይናገር ከመጽሐፋቸው ብዙ ሐሳብ ወስዶአል:: ለምሳሌ መጽሐፉ እጅግ አብዝቶ የጠቀሰው፣ የ"ፖጋኒዝም ኢን አወር ክርስቲያኒቲ" ጸሓፊ አርተር ዌግል ትምህርተ ሥላሴ ብቻ ሳይሆን የጌታ ራት፣ የውሃ ጥምቀት፣ የድንግል መፀነስና መውለድ ወዘተ ሁሉ፣ ከአረማውያን መድብለ አማልክት ትምህርት የተወሰደ ነው የሚል ትምህርት አለው[28]:: ዌግል የይሖዋ ምስክሮችም ሆኑ ክርስቲያኖች የሚያምኗቸውን መጽሐፍ

---

[26] ለምሳሌ የራሱ የመጠበቂያ ግንብ መምህራን፣ ክርስታደልፊያን በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት ጸሓፍያን፣ እንዲሁም ዘ ዌይ ኢንተርናሽናል በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት አባላት ይገኙበታል::

[27] የመስኩ ምሁራንን እማኝነት በመጥቀስ ሙግትን ማጠናከር ርቱዕ ለሆነ ሙግት ትክክለኛ አካሄድ ቢሆንም፣ የራስን አስተምህሮ ለማጽናት የራስን ሰዎች በእማኝነት መጥቀስ ግን ስሕተት ነው ("የቤተ ክርስቲያኔ አስተምህሮ ትክክል ለመሆኑ የቤተ ክርስቲያኔ መጋቢ እማኝነቱን ይስጥልኝ" እንዴት ይባላል?)::

[28] Arthur Weigall, *The Paganism in Our Christianity*, 1928. [The Twelve Disciples Derived From Zodiac: p25. The 27 books of the New Testament Canon is invalid: p37. The name Mary is of pagan origin: p41, The virgin birth is of pagan origin: p44, 47, 60. The early life of Jesus is totally unknown: p49. Jesus born in a stable and wrapped in swaddling clothing is of pagan origin: p52. Miracles of Jesus are of pagan origin: p58. Jesus' 40 day temptation in wilderness is of pagan origin: p61. Earthquake at cross is false: p62. Jesus Crucifixion was a Jewish human sacrifice of pagan origin: p69,76. Jesus Side Pierced is of pagan origin: p83,84. Jesus never actually died, two angels were only men: p93,94. Ascension is of pagan origin: p100. Jesus suffering to save us is of pagan origin: p106. Jesus decent into Hades is of pagan origin: p113. Jesus "hung on a tree" is of pagan origin: p118. Jesus the "Rock of salvation" is of pagan origin: p129. Jesus the "slain Lamb of God" is of pagan origin: p131,132. "Washed in the Blood of the lamb" is of pagan origin: p132. Baptism and the Lord's Supper are both of pagan origin: p134, p146,147. Phrase "Soldiers of Christ" is of pagan origin: p135. Jesus as "the Shepherd" is of pagan origin: p136. Lords Supper is of pagan origin" p146,147. The idea of "blood atonement for sins" is of pagan origin: p152,158. Jesus "Begotten of God" is of

ቅዱሳዊ ትምህርቶች ሁሉ የማይቀበል ጸሓፊ ነው:: እንዲያውም ጸሓፊው የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚህች ምድር ከመምጣቱ በፊት ሊቀ መላእክ ሚካኤል ነው የሚለው ትምህርታቸው ራሱ አረማዊ መሠረት አለው ሲል ጽፎአል:: እንደ አርተር ዌግል ሁሉ ጆን ራይላንድስ[29]፣ ኢ. ዋሽበርን ሆፕኪንስ[30]፣ ሲግፍሬንድ ሞሬንዜ[31]፣ ዊል ዱራንት[32]፣ ሌይማን አቦት[33]፣ ኤድዋርድ ጊቦን[34]፣ አዶልፍ ሃርናክ[35] ወዘተ መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ መሠረታዊ በሚባሉት ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች የማያምኑ የክርስትና መሠረተ እምነት ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አምልኮ የተቀዳ ነው የሚል ጽኑ አቋም ያላቸው ናቸው::

በአጠቃላይ የመጠበቂያ ግንብ የሥላሴ አስተምህሮ እንዲቃወሙለት የጠቀሳቸው እነዚህ ጸሓፍያን ትምህርተ ሥላሴን ጨምሮ ትንሣኤ ሙታን፣ መጽሐፍ ቅዱስ አፊዎተ እግዚአብሔር መሆኑን፣ የድንግል መፀነስ የዘላለም ቅጣት፣ ከሞት በኋላ ቅዱሳን ስለሚያገኙት የሕይወት አክሊል ወዘተ ከአረማውያን መድብለ አማልክት አስተምህሮ በቀጥታ የተወሰደ ነው የሚል ክስ በክርስትና ሃይማኖት ላይ የሚያቀርቡ ናቸው:: ድርሰታቸውም ይኸው ጉዳይ እውነት መሆኑን የሚመግት ነው:: 99 በመቶ የሚሆነው የእነዚህ ጸሓፍያን አቋም፣ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ከየትኛውም የቤተ ክርስቲያን አቋም ጋር የሚስማማ አይደለም:: ይህ እውነት በሆነበተ ሁኔታ ይህ ዐይነቱ መሪር ጥላቻና ቅድመ ዝንባሌ ያላቸውን ግለሰቦች መጽሐፍ በመጥቀስ፣ "ትምህርተ ሥላሴ ከአረማውያን መድብለ አማልክት አስተሳሰብ በቀጥታ የተወሰደ ነው" ማለት ስሕተት ነው:: ድርጅቱ እነዚህ ግለሰቦች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም፣ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዲያውም እግዚአብሔር የሚባል ነገር የለም የሚለውን ትምህርታቸውንና ሙግታቸውንስ ይቀበላልን?

በአጠቃላይ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ከጠቀሳቸው 33 ጥቅሶች መኻል 8ቱ (25%) በህልዎተ እግዚአብሔር የማያምኑ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ መሠረታዊ የሚባሉትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች የማይቀበሉ እንዲያውም እነዚህ አስተምህሮዎች አረማዊ መሠረት ያላቸው የሚሉ ጸሓፍት ናቸው:: 2ቱ (6%) አርዮሳዊ አመላከከት ያላቸው ጸሓፍያን/የድርጅቱ መምህራን ናቸው:: 3ቱ (10%) የይሁዲ እምነት፣ የሂንዱ እምነትና ሙስሊም ጸሓፍያን ናቸው:: 4ቱ (12%) አንዳችም ሃይማኖታዊ ዝንባሌ የሌላቸው ጸሓፍት ቢሆኑም ጽሑፋቸው ትክክለኛ በሆነ መልኩ ተጣቅሶ አልቀረበም:: 16ቱ (50%) የሥላሴ አማንያን ሲሆኑ፣ የግለሰቦቹ ሐሳብ በተዛባ መልኩ እየተበጣጠሰ ቀርቦአል[36]::

---

pagan origin: p169. Incarnate Logos of Jn 1:1 is of pagan origin, The "pre-existent angel" is a 4th century concept: p172,173-175. ***The Trinity is of pagan origin: p182***. The "Lord's Day" (Sunday) is of Pagan Origin: p209,210-211. Jewish Sabbath and the Sunday Lord's Day both of pagan origin: p136, p209,210-211. Conclusion of entire book: Almost all of Christianity is of pagan origin! p242]

[29] John Rylands, *Bulletin of The John Rylands Library* (G.H. Boobyer, "Jesus as 'Theos' in the New Testament," *Bulletin of the John Rylands Library* 50, 2(Spring 1968): 251.

[30] E. Washburn Hopkins, *The Origion and Evolution of Religion* (New Haven, Conn.: Yale University Press, 1923).

[31] Siegfriend Morenz, *Egyptian Religion*

[32] Will Durant, *The Story of Civilization*

[33] Lyman Abbott, *Dictionary of Religious Knowledge*

[34] Edward Gibbon, *Bulletin of The John Rylands Library*

[35] Adolf Harnack, *Outlines of the History of Dogma*

[36] እያንዳንዱ መረጃ እንዴት ተዛብቶ እንደ ቀረበ በተጫባጭ ለማስተዋል የሚከተለውን ድረ ገጽ ይመለከቷል <http://www.bible.ca/trinity/trinity-jw-deceptions>::

## III. ሁለት አማራጮችን ብቻ በማቅረብ ወደ ድምዳሜ መድረስ

ይህ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር መጽሐፍ፣ ለትምህርቱ ማጐላበቻ የወሰዳቸውን ምንጮች ያብራራው ሁለት ብቸኛ የትንታኔ አማራጮች ብቻ እንዳሉ አድርጎ በማቅረብ እንዲሁም ሦስተኛ አማራጭ እንደሌለ በማሳየት ሰዎች ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ እንዲሄዱ ያደርጋል[37]:: ለምሳሌ የሥላሴ ጸሐፍያን ኢየሱስ ለአብ ይገዛል ያሉባቸውን ምንጮች በመጥቀስ ኢየሱስ ለአብ ከተገዛ አምላክ ያለመሆኑን፣ ከአብ ማነሱን ወይም ፍጡር መሆኑን ያሳያል ወደሚለው ድምዳሜ እንዲደርሱ ያደርጋል:: ነገር ግን መገዛት ማነስን የማያሳይባቸው ሁኔታዎች አሉ:: "ሚስቶች ለባሎቻቸው ይገዙ" ወይም "የነቢያት መንፈስ ለነቢያተ ይገዛል" የሚለው ቃል በፈቃደኝነት መታዘዝን እንጂ በባሕርይ/በተፈጥሮ ማነስን የሚያሳይ አይደለምና ይህን ሐሳብ በነገረ መለኮት ትንተና ወቅት በስፋት የምንመለከተው ይሆናል::

## IV. ምንጮችን በትክክል ያለመጥቀስ

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት፣ በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? በሚል ርእስ ያሳተመው መጽሐፍ ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው የሥላሴን ትምህርት እንዳላስተማሩ እንዲያውም እነዚህ አባቶች አርዮሳዊ አመለካከት እንደ ነበራቸው የሞገተው የታሪክ ድርሳናትን በመጥቀስ ቢሆንም ከሌሎቹ የመጽሐፍቱ ክፍሎች በተለየ መልኩ የጠቀሳቸውን እማኞች ምንጭ አልጠቀሰም::

የቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው የግሪክ ጽሑፎች እጅግ በርካታ ከመሆናቸውም በሁለት ጸሐፍያን በጣምራ የተዘጋጁ 7 ተከታታይ ቅጽ ያላቸው መጻሕፍት አሉ[38]:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የመጠ መቂያ ግንብ ድርጅት ከእነዚህ ጽሑፎች ጠቀስኋቸው የሚላቸውን አንድና ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ይህን ያህል ስፋት ካለው ጽሑፍ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት ከሣር ክምር ውስጥ መርፌ ከመፈለግም በላይ እጅግ ከባድ ነው:: ይህ በግልጽ በሚታወቅበት ሁኔታ እንዲሁም ምንጭን ጠ ቅሶ መጻፍ ግዴታ ያለመጻፍ ደግሞ ወንጀል በሆነበት ምሁራዊው ዓለም ድርጅቱ ይህን አካሄድ መምረጡ ለምን ይሆን?

## ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ምን አስተማሩ?

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው በቀጥታ ጠ ቅሻቸዋለሁ ያላቸው ስፍራዎች በትክክል እንዲታወቁ ቢያደርግ ኖሮ፣ የጠቀሳቸውን ክፍሎች አንድ በአንድ እየነቀስን በማውጣት የጉዳዩን እውነተኛነትም ሆነ ስሕተት በቀላሉ መመርመር በቻልን ነበር:: ድርጅቱ ግን ምንጩን በመደበቅ ይህን ዕድል ነፍጐናል::

እውነታውን ለመመርመር የቀረልን ብቸኛ አካሄድ ድርጅቱ በሥላሴ አያምኑም አርዮሳዊ አመለካከት ነበራቸው ያላቸውን ግለሰቦች ጽሑፍ በቀጥታ በመተርጐም "መረጃው ራሱ ይናገር" ማለትን መርጣናል:: አንባብያን መረጃው ከአዘንብሎት ፍጹም የጠራ መሆኑን በቀላሉ ይረዱ ዘንድ ምንጮቻችንን በትክክል ሥርዐቱን ጠብቀን ለመጥቀስ ሞክረናል::

---

37 ይህ በሥነ አመክንዮ "False Dilemmas" በመባል ይታወቃል::

38 *Apostolic Constitutions.* Edited by Alexander Roberts and James Donaldson 7 Vol. New york: Charles Scribner's Sons, 1899.

በዚህ ጳሰሳዊ ጥናት ውስጥ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የሥላሴያዊ አስተምህሮ ያልነበራቸው አርዮሳዊ አባቶች ነበሩ በማለት ያቀረባቸው አበው ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ ምን ዐይነት አቋም እንደ ነበራቸው ማሳየት እንጂ ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ሥላሴን አስመልክቶ የነበራቸውን አስተመህሮ መተንተን አይደለም[39]:: ስለዚህ ድርጅቱ ያቀረባቸውን አባቶች ብቻ የትምህርታቸው መሠረት ምን እንደ ሆነ ለማየት ሙከራ እናደርጋለን::

አስገራሚው ጉዳይ ግን፣ በትምህርተ ሥላሴ ላይ በተለይም በክርስቶስ አምላክነት ላይ ሰፊ ትምህርት ያቀረቡትን የቅድመ ኒቂያ ጉባኤ አበውን የይሖዋ ምስክሮቹ መጽሐፍ ያለ መጥቀሱ ነው:: ለምሳሌ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት የነበረውና በ98 ዓ.ም ወይም በ117 ዓ.ም እንደ ሞተ የሚገመተው አግናጢዮስ የክርስቶስን አምላክነት በተመለከተ ከየትኛውም ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ይልቅ ሰፊ ትምህርት አቅርቦአል:: ነገረ ግን ይህ የቤተ ክርስቲያን አባት የመጠበቂያ ግንብን መስፈርት ማሟላት ስላልቻለ "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ እንዳይካተት ተደርጐአል:: ምናልባትም ድርጅቱ የሌሎችን አባቶች ጽሑፍ አጣሞ እንዳቀረበው የዚህን ስመ ጥር አባት ጽሑፍ ለማጣመም አስቸጋሪ ሆኖ ስላገኘው ይሆናል:: የመጽሔቱን መስፈር ማሟላት ስለተሳናቸው በድርጅቱ መጽሐፍ ላይ ካልተጠቀሱት ውስጥ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የአስተምህሮና የሥርዐተ አምልኮ መጽሐፍ የሆነው ዲዳኬ (ትምህርተ ሐዋርያት)፣ የሮሙ ቀለሜንጦስ፣ ጳሊቃርጶስ፣ ሔርማስና ጳጲያስ ይገኙበታል::

የመጠበቂያ ግንብ መጽሔት:—

> ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩት አባቶች ከክርስቶስ ልደት በኋላ በነበሩት በመጀመሪያዎቹ መቶ ዘመናት ግንባር ቀደም የሃይማኖት መምህራን እንደ ነበሩ ይታወቃል:: እነዚህ መምህራን ያስተማሩትን ማወቅ ጠቃሚ ነው (በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ገጽ 7)::

የሚል አቋም እስካለው ድረስ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ ከላይ የጠቀስናቸውን የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ምስክርነት ማቅረብ የሚኖርበት ይመስለናል::

በይሖዋ ምስክሮች ድርጅትና አስተምህሮ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ምሁራን እንደሚያስረዱት[40]፣ ድርጅቱ ይህን ትችት ለመከላከል እንዲሁም የመጽሐፉን ሙግት ለማጐላበት መጽሐፉ ከታተመ ከሁለተ ዓመት በኋላ በመጠበቂያ ግንብ መጽሔት ላይ በአግናጢዮስ ዘአንጾኪያ[41] ላይም ሆነ በመጽሐፉ ላይ በጠቀሳቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ላይ[42] ሙግቴን ያጠናክርልኛል ያላቸውን መረጃዎች እንደ ልማዱ ምንጫቸውን ሳይጠቅስ ለማቅረብ ሙከራ አድርጎአል::

## ዮስጦስ ሰማዕት

*"በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?"* በሚል ርእስ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ያሳተመው መጽሐፍ ዮስጦስ ሰማዕት ኢየሱስ ክርስቶስ:— (1) ከአብ የተለየ ማንነት

---

[39] ተስፋዬ ሮበሌ፣ *የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፣ አዲስ አበባ፣ 1998 ዓ.ም)፣ 17-21::

[40] James White, *"Historical Honesty and the Watchtower Society"* (በሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ሙሉ ጽሑፉን ማግኘት ይቻላል:- http://www.aomin.org/Witnesses.html).

[41] ዝኒ ከማሁ ከ*መጠበቂያ ግንብ፣* February 1, 1992 ገጽ 19-23 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[42] ዝኒ ከማሁ ከ*መጠበቂያ ግንብ፣* November 1, 1991 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

እንዳለው፣ (2) በአብ የተፈጠረ መልአክ እንደ ሆነ፣ (3) በማንነቱ ከአብ እንደሚያንስ እንዲሁም፣ (4) አንደ አብ ሁሉን ነገር የማድረግ ችሎታ እንደ ሌለው የሚያምን የቤተ ክርስቲያን አባት ነው ሲል ሞግቶአል:—

> በ165 እዘአ በሰማዕትነት የሞተው ጀስቲን ኢየሱስ ሰው ከመሆኑ በፊት፣ "ሁሉን ከፈጠረው እግዚአብሔር የተለየና" የተፈጠረ መልአክ እንደ ሆነ ገልጾአል። በተጨማሪም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ያነሰ እንደ ነበረና "ፈጣሪ እንዲናገርና እንዲሠራ ከፈቀደለት ውጭ ምንም ነገር የማያደርግ. . ." እንደ ነበረ ተናግሯል[43]።

ዮስጦስ ሰማዕት ኢየሱስ ከአብ የተለየ ማንነት አለው ብሎአል የሚለው ንግግር ከሥላሴ አማንያን መሠረተ እምነት ጋር አንድ ቢሆንም (የባሕርይ/የተፈጥሮ ማንስ ሳይሆን የሥራ ክፍፍል ማነስ)፣ በአብ የተፈጠረ መልአክ ነው፣ ከአብ የሚያንስ ማንነት አለው፣ እንዲሁም እንደ አብ ከሃሌ ኩሉ (ሁሉን ቻይ) አይደለም የሚለው ገለጻ ግን የዮስጦስን እምነት በጭራሽ የሚወክል አይደለም። ድርጅቱ ስለ ዮስጦስ ሰማዕት ካቀረበው ገለጻ በተለየ መልኩ ዮስጦስ ስለ ኢየሱስ የሚከተለው እምነት ነበረው[44]:—

> "የዓለማት ፈጣሪ እግዚአብሔር ልጅ አለው፤ ይህ ልጅም በኩር የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ እንዲሁም እግዚአብሔር ነው። በጥንቱ ዘመን በእሳት አምሳል በመላእክት ገጽ ለሙሴ እንዲሁም ለተቀሩት ነቢያት ተገልጾ ነበር"[45]።

በሌላ ስፍራ ደግሞ ዮስጦስ ኢየሱስ:—

> "የሰራዊት ጌታና አምላክ ነው"[46]። "የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ እግዚአብሔር ነው"[47] ይላል።
>
> "ኢየሱስ አምላክና የሰራዊት ጌታ ተብሎአል"[48]
>
> "በመዝሙር መጽሐፍ አርባ ስድስተኛው መዝሙር ስለ ክርስቶስ እንዲህ ይላል:- 'እግዚአብሔር በእልልታ ከፍ ከፍ አለ፤ ጌታ በመለከት ድምፅ'"[49]
>
> [ትሪፎ[50] ለዮስጦስ እንዲህ ይለዋል]:- "... ይህ ክርስቶስ ልክ እንደ እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ነበረ እያልከኝ ነው ያለህው፤ ከዚያም ሰው ሆኖ ለመወለድ በመፍቀዱ ምክንያት ሰው ሆነ ነው የምትለው"[51]

---

43 *"በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?"* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993), 7.

44 "ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ምን አስተማሩ?" በሚለው ርእስ ሥር በርካታ መረጃዎችን የወሰድነው Robert M. Bowman, Jr. *Why You Should Believe in the Trinity: An Answer to Jehovah's Witnesses* (Grand Rapids: Baker Books, 1989), 27-47 ላይ ነው።

45 Justin Martyr, *First Apology* 63, in *The Ante-Nicene Fathers: Translations of the Writings of the Fathers down to A.D. 325,* ed. Alexander Roberts and James Donaldson, rev.ed. A. Cleveland Coxe (Grand Rapids: William B. Eerdmans Publishing Co., 1969 reprint [orig. 1885]), 1:184. ከዚህ በኋላ ይህን መጽሐፍ *ANF* በሚል ምኅጻረ ቃል ብቻ እንጠቅሰዋለን።

46 Justin Martyr, *Dialogue with Trypho* 36, in *ANF,* 1:212.

47 ዝኒ ከማሁ፤ 128, in *ANF,* 1:264.

48 ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho ch. 36.

49 ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho, ch. 37.

50 ከዮስጦስ ጋር ይወያይ የነበረ አይሁዳዊ ነው።

51 ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho, ch.48.

"ትሪፎም እንዲህ ሲል መለሰለት '...እግዚአብሔር ሰው ለመሆንና ለመወለድ ታገሠ...እኛ የጠቀስናቸው አንዳንድ ቅዱሳት መጻሕፍት መሲሕ እንደሚሠቃይ የሚያረጋግጡ ናቸው፤ እንዲሁም እንደሚመለክ፣ አምላክ እንደ ሆነ፣ እስካሁን የነገርሁህ በርግጥ መሲሑን የሚያመለክቱ ናቸውን'"[52]

ዮስጦስ ዕብራውያን 1÷8 በመጥቀስ የክርስቶስን አምላክነት በዚህ መልኩ ያስረግጣል:- "...አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ነው"[53]

"እነዚህ ቃላት በግልጽ እንደሚያሳዩት እርሱ ክርስቶስ ይህን ነገር በመሠረተው በእርሱ ተመስክሮለታል፣ ይኸውም አምላክና ክርስቶስ እንደ መሆኑ መጠን አምልኮ ይገባዋል"[54]።

"አሁን በረጅሙ ያረጋገጥነው ነገር ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ነው"[55]

እንዲያውም ዮስጦስ በትምህርተ ሥላሴ ላይ ያለውን እምነት በሚከተለው መልኩ ገልጾአል:—

"ክርስቲያኖች አግዚአብሔር አብንና ወልድን. . .እንዲሁም ነቢያዊ የሆነው መንፈስ ያመልካሉ"[56]።

ይህም የክርስቲያኖች እምነት የአሐዱ አምላክ እምነት እንጂ፣ ሦስት አማልክትን ማምለክ እንዳልሆነ ገልጾአል:—

"እግዚአብሔርን ብቻ ልናመልክ ይገባናል. . .ስግደት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነውና"[57]።

ዮስጦስ ሰማዕት በጽሑፎቹ ውስጥ ኢየሱስን መላእክ ያለበት ሁኔታ አለ። ይህ ግን መጠበቂያ ግንብ ድርጅት እንደሚያምነው ኢየሱስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው ለማለት ሳይሆን፣ (1) ኢየሱስ በአብ የተላከ መልእክተኛ (መልአክ) ነው ለማለት እንዲሁም፣ (2) የአብ መልእክተኛ ሆኖ ወደዚህች ምድር ከመምጣቱ በፊት ማለትም በዘመነ ብሉይ እንደ እግዚአብሔር መልአክ በመሆን ለቅዱሳን እንደ ተገለጠ ለማስረዳት ነው። እነዚህ ሁለት ሐሳቦች በርካታ የሥላሴ አማንያን ራሳቸው ከሙሉ ልብ የሚቀበሉት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከሥላሴ አስተምህሮ ጋር አንዳችም ቅራኔ የሌለበት አመለካከት ነው። ዮስጦስ ይህን ማለቱ ትምህርተ ሥላሴን የማይቀበል ነው ወይም አርዮሳዊ አመለካከት ነበረው ማለት በጭራሽ አይቻልም።

የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር:—

በ165 እዘአ በሰማዕትነት የሞተው ጀስቲን ኢየሱስ ሰው ከመሆኑ በፊት፣ "ሁሉን ከፈጠረው እግዚአብሔር የተለየና" የተፈጠረ መልአክ እንደ ሆነ ገልጾአል። በተጨማሪም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ያነሰ እንደ ነበረና "ፈጣሪ እንዲናገርና እንዲሠራ ከፈቀደለት ውጭ ምንም ነገር የማያደርግ. . ." እንደ ነበረ ተናግሯል[58]።

በለው ጽሑፉ ውስጥ:—

የተፈጠረ መልአክ እንደ ሆነ ገልጾአል። በተጨማሪም ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ያነሰ እንደ ነበረና

[52] ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho, ch. 68.
[53] ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho ch. 56.
[54] ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho, ch. 63.
[55] ዝኒ ከማሁ፤ Dialogue with Trypho, ch. 124.
[56] Justin Martyr, *First Apology 6*, in *ANF*, 1:164.
[57] ዝኒ ከማሁ፤ 16, 17, in *ANF*, 1:168.
[58] *"በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?"* (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993), 7.

የሚለው ሐረግ ለድርጅቱ ሙግት ዋነኛ ቢሆንም፣ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ያለመግባቱን ግን ልብ ይሏል።

ስመ ጥር የቤተ ክርስቲያን ዐቃቤ እምነት[59] የነበረና በ100 ዓ.ም ተወልዶ 165 ዓ.ም በሰማዕትነት የሞተው ዮስጦስ ሰማዕት፣ ሥላሴ የሚለውን ሙያዊ ቃል ያልተጠቀመ እንዲሁም አብና ወልድ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን በተፍታታ መልኩ ያላስቀመጠ ቢሆንም ዮስጦስ ለአብ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ እንዳደሚሰግድ፣ ኢየሱስም ፍጹም አምላክ እንደ ሆነ የገለጸ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።

## ሔሬኔዎስ

*"በሥላሴ ማመን ይገባሃል?"* የሚለው የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ሔሬኔዎስ፡— (1) ኢየሱስ ከአብ የተለየ ማንነት እንዳለው እንዲሁም (2) በማንነቱ ከአብ ያነሰ ባሕርይ እንዳለው ገልጾአል የሚል ትምህርት አለው፡—

> ኢየሱስ ሰው ከመሆኑ በፊት ከእግዚአብሔር የተለየና ያነሰ ሕልውና እንደ ነበረው በ200 እዘአ አካባቢ የሞተው ኢረንየስ ተናግሯል። ኢየሱስ "ከአንዱ እውነተኛና ብቸኛ እግዚአብሔር" ማለትም "የሁሉም የበላይ ከሆነውና ሌላ እኩያ ከሌለው አምላክ" ጋር እኩል እንዳልሆነ አምልክቶአል። (ገጽ 7)

እዚህ ላይ ልብ ልናደርግ የሚገባን አራት መሠረታዊ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም፡— (1) የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከሔሬኔዎስ ጽሑፍ ነው ብሎ የጠቀሰው ጥቅስ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን የሚገልጽ አንዳችም ነገር የለውም። የሥላሴ አማንያን ራሳቸው አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ከሙሉ ልብ የሚቀበሉ ቢሆንም እንኳ፣ ድርጅቱ ከሔሬኔዎስ ጽሑፍ ጠቀስሁት የሚለው ክፍል ግን ይህን የሚያስረዳ አንዳችም ፍንጭ የለውም። (2) የመጠበቂያ ግንብ ድርጅቱ የሔሬኔዎስ ሐሳብ ነው ብሎ የጠቀሰው ክፍል በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀመጠና በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ያልተቀመጡ ነገሮችን ቀያይጦ አቅርቧል። አንባቢ ልብ እንዲለው የምንፈልገው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ የቀረበው ሐሳብ ሳይሆን ከትእምርተ ጥቅሱ ውጪ የተጻፈው ሐሰብ ነው። ከዚህ የምንግረው ጉዳይ ሔሬኔዎስ ቃል በቃል፣ አብ ከወልድ "ጋር እኩል እንዳልሆነ አመልክቶአል" የሚለው ሐሳብ የሔሬኔዎስ ትምህርት ያለመሆኑን ነው። (3) ሔሬኔዎስ አብ ከወልድ ጋር እኩል አይደለም የሚል ሐሳብ አለው እንኳ ብንል፣ ይህ "እኩል አይደለም" የሚለው ሐሳብ ራሱ ማብራሪያ የሚፈልግ እንጂ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት እንደሚለው፣ "አብ ፈጣሪ ወልድ ደግሞ ፍጡር

---

[59] ዐቃቤ እምነት/ክርስትና የሚለው ስያሜ (Apologetics) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚወክል ነው። በግእዝ ዐቃቢ ማለት የሚጠብቅ፣ ጠባቂ፣ ተመልካች፣ ከልካይ ማለት ነው። ዐቃቤ ክርስትና የሚባሉት የክርስትናን መሠረተ እምነት ከመናፍቃን እንዲሁም ክርስቲያናዊ ካልሆኑ የተለያዩ የስሕተት ትምህርቶች/ሒሶች የሚጠብቁ ሰዎች ናቸው። *"አፖሎጄቲክስ"* (apologetics) ይሚለው የእንግሊዝኛ ስያሜ የተወሰደው *"አፖሎጂያ"* ወይም *"አፖሎጂዮ"* ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። አፖሎጂያ የሚለው ቃል በ1ጴጥሮስ 3÷15 ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ ሁሉም የአማርኛ ትርጉሞች (የ1954፣ የ1980 እንዲሁም የአዲሱ መደበኛ ትርጉም) *"መልስ መስጠት"* ብለው ተርጉመውታል። በአብዛኛው ይህ ክፍል ለዐቃቤ ክርስትና መሪ ጥቅስ ተደርጎ ይወሰዳል። የዐቃቤ ክርስትና ዐቢይ ዐላማ፣ ክርስቲያናዊ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ምክንያታዊ/ምክንዩአዊ ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ነው። አፖሎጂያ የሚለው የግሪክ ቃል በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥም ተጠቅሶ ይገኛል (ሐዋርያት ሥራ 22÷1፤ 25÷16፤ 1ቆሮንቶስ 9÷3፤ 2ቆሮንቶስ 7÷11፤ ፊልጵስዩስ 1÷7:16፤ 2ጢሞቴዎስ 4÷16)።

መሆኑን የሚያመለክት ነው" ወደሚለው ድምዳሜ የሚወስድ አይደለም። የሥላሴ አማንያንም ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኀጢአት ሲል ሰው በመሆኑ ከአብ ዝቅ እንዳለ፣ ሰው በመሆኑ ከኀጢአት በስተቀር ከሰው ጋር እኩል እንደ ሆነ ሁሉ አምላክም ስለሆነ ከአብ ጋር እኩል ነው። በአጠቃላይ ወልድ ለአብ ራሱን ዝቅ ማድረጉ የአምላክነት ባሕርይ የለውም ወደሚለው ድምዳሜ ድምዳሜ የሚያደርሰው የተጠቀሰበት ዐውድ ይህ ዐይነቱ ትምህርት ሲኖረው ብቻ ነው። (4) ሔሬኔዎስ "እውነተኛና ብቸኛ የሆነውን እግዚአብሔር" ከኖስቲኮች ሐሳዊ አምላክ ጋር በማነጻጸር የኖስቲኮች አምላክ አምላክ አይደለም ያለበት ሁኔታ አለ። ይህ ንጽጽር የተካሄደው ግን በአብና በወልድ መካከል ሳይሆን በአብና በኖስቲኮች አምላክ መካከል ነው።

አስደናቂው እውነት ግን ሔሬኔዎስ ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ የነበረው ትምህርት ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከምታስተምረው የሥላሴ ትምህርት ቅንጣት ያልተለየ ለመሆኑ ጥቂት ናሙናዎችን ቈንጥረን እንመልከት:—

> "ቤተ ክርስቲያን፣ የሰማይ፣ የምድርና የባህር በውስጣቸውም የሚኖሩ ሁሉ ፈጣሪ በሆነው፣ ሁሉን በሚችለው አምላክ በአብ፣ ለድነታችን ትስብእት በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በወልድ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ዘመን በነቢያቱ በኩል ባወጀው በመንፈስ ቅዱስ ታምናለች"[60]።

በዚሁ ዐውድ ውስጥ ሔሬኔዎስ ኢየሱስን:—

> "ጌታችን፣ አምላካችንና ንጉሣችን ክርስቶስ ኢየሱስ"[61]

> "የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ የፍጥረቱ አካል ለመሆን ከድንግል ማርያም ለመወለድ የወረደ ሰውን ከራሱና ከእግዚአብሔ ጋር ያስታረቀ"[62]

ብሏል። እንዲሁም:—

> "ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ እንዲሁም እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ብትበተንም፣ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያትና ከእነርሱ ደቀ መዛሙርት የተቀበለችው የሚከተለውን መሠረተ እምነት ነው:- ሁሉን ቻይ የሆነና ሰማይንና ምድርን እንዲሁም ባሕርን በእነዚህም ውስጥ የሚኖሩትን ሁሉ የፈጠረ አንድ እግዚአብሔር፤ በእግዚአብሔር ልጅ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለድነታችን ሲል ትስብእት የሆነ፤ በመንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔርን ዘመን በነቢያቱ ያበሠረ እንዲሁም የተወዳጁ ጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት፣ ከድንግል መወለድ፣ ሕማም፣ ከሙታን መነሣት፣ በአካለ ሥጋ ወደ ሰማይ ማረግ፣ 'ሁሉን አንድ አድርጎ ለመሰብሰብ' በአብ ክብር ከሰማይ መገለጥ፣ የሰው ልጆችን ሁሉ በአዲስ አካል ከሙታን ማስነሣት፣ ይኸውም ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታችንና አምላካችን እንዲሁም አዳኛችንና ንጉሣችን መሆኑን፣ በማይታየው አብ ፈቃድ 'በሰማይና በምድር ከምድርም በታች' ያለ ጕልበት ሁሉ እንዲንበረከክለት፣ ምላስም ሁሉ ለሁሉ ኀጢአት ብሎ እንደ ተሰዋ እንዲመሰክርለት ነው. . ."[63]

> "ነገር ግን ወልድ ከዘላለም ዓለም ጀምሮ ከአብ ጋር አብሮ የነበረ ነው"[64]

[60] Irenaeus, *Against heresies* 1.10.1 in *ANF,* 1:330.
[61] ዝኒ ከማሁ፤ in *ANF,* 1:417.
[62] Clement of Alexandria, *Exhoration to the Heathen* 10, in ANF, 2:202.
[63] Irenaeus, *Against heresies* X.l in *ANF,* 1:330.
[64] Against Heresies, Book II, ch. 30, section 9.

"ወልድ ለሙሴ ሲናገር እንዲህ ብሏል፣ 'ይህንን ሕዝብ ልቤኸው ወርጃለሁ' (ዘፀአት 3÷8--በሚቃጠለው ቁጥቋጦ) ይህ ለሰው ልጆች ድነት ወደ ላይ የሚወጣውና ወደታች የሚወርደው እርሱ ነው"[65]።

"ሁሉን ነገር የፈጠረው እርሱ ከቃል ጋር ብቻውን ነው ያለው፤ አምላክና ጌታ ተብሎ ይጠራል። የተፈጠሩ ፍጡራን ግን ይህ ዐይነቱ ቃል ለእነርሱ መጠሪያ ሊሆን አይችልም፤ ፍትሓዊ በሆነ መልኩም የይገባኛል ጥያቄ ሊያቀርቡ አይችሉም፤ ይህ መጠሪያ የፈጣሪ መጠሪያ ብቻ ነውና"[66]
"ከቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንዳሳየሁት፣ በሁሉ ነገር ፍጹም በሆነ ሁኔታ የአዳም ልጅ የሆነ እግዚአብሔር ተብሎ ሊጠራ ወይም ጌታ የሚባል ስም ሊሰጠው አይችልም። እርሱ ግን በራሱ ሥልጣን እስካሁን ከኖሩ ሰዎች በበለጠ መልኩ አምላክ፣ እንዲሁም ጌታ እንዲሁም ዘላለማዊ ንጉሥ፣ እንዲሁም ትስብእት የሆነ ቃል፣ በነቢያት ሁሉ፣ በሐዋርያት ሁሉ፣ እንዲሁም በራሱ በመንፈስ እንኳ የታወጀ. . .ቅዱሳት መጻሕፍት ስለእርሱ ይህን ነገር የማይመሰክሩ ከሆነ እንደ ሌላው ሁሉ ሰው ብቻ በሆነ ነበር"[67]።

"ስለዚህ ክርስቶስ ራሱ ከአባቱ ጋር ለሙሴ የተናገረ የሕያዋን አምላክ ነው፤ እንዲሁም አብን የገለጠው እርሱ ነው"[68]።

"[በምድር ላይ] በተገኘበት ጊዜ ሁሉም ስለ ክርስቶስ ተናገሩ፤ እርሱንም አምላክ አሉት"[69]።

"ሰውን የፈጠረው እግዚአብሔር እንጂ. . .መላእክት አይደሉም፤ ስለዚህ የፈጠረን ማነው. . .የመላእክት ኀይል የእግዚአብሔርን መልክ/አምሳል ሊፈጥር አይችልም"[70]።

"ነቢያት የነቢይነትን ስጦታ የሚያገኙት ከዚያው ከቃል ነው፤ ሥጋ ሆኖ እንዲሁም በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ አምላክና ሰው ሆኖ እንደሚመጣ ዐወጁ፤ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚመጣ፣ እግዚአብሔርም ለሰው ልጆች እንደሚታይ እንዲሁም በምድር ላይ ከሰው ልጆች ጋር እንደሚወያይ ቀድሞውኑ ተነግሮአል"[71]።

"ቃል ማለትም ወልድ ከአብ ጋር ዘወትር አለ"[72]።

"አንድ እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አምላክ የለም። እርሱም ሁሉን ፈጠረ። እርሱ ብቻውን አምላክ፣ እርሱ ብቻውን ጌታ፣ እርሱ ብቻውንም ፈጣሪ ነው"[73]።

"ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ለፍጥረቱ ካለው ከታላቅ ፍቅር የተነሣ ከድንግል ለመወለድ ወረደ"[74]።

---

[65] *Against Heresies,* Book III, ch. 6, section 2.
[66] *Against Heresies,* Book III, ch. 8, section 3.
[67] *Against Heresies,* Book III, ch. 19, section 2.
[68] *Against Heresies,* Book IV, ch. 5, section 2 (12).
[69] *Against Heresies,* Book IV, ch.6, section 6. **በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።**
[70] *Against Heresies,* Book IV, ch. 20, section 1 (13).
[71] *Against Heresies,* Book IV, ch. 20, section 4
[72] *Against Heresies,* Book IV, ch. 20, section 3.
[73] *Against Heresies,* Book II, ch.1, section 1.
[74] *Against Heresies,* Book III, ch. 4, section 2

ሔሬኔዎስ የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ከነበረው ከፖሊቃርጶስ እግር ሥር የተማረ ሰው ስለሆነ በኢየሱስ አምላክነት ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ ምን ዐይነት አቋም ነበረው የሚለውን ነገር ማወቅ የሔሬኔዎስ ኢየሱስን በተመለከተ ያለውን አስተምህሮ ለማወቅ ይጠቅማል (ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ)[75]:: ሔሬኔዎስ ራሱ ዮሐንስ 1÷1 በመጥቀስ እንዲሁ ብሏል:—

> " '...ቃልም እግዚአብሔር ነበር' ከእግዚአብሔር የተወለደ እግዚአብሔር መሆኑ እርግጥ ነው"[76]

በአጠቃላይ በ115 ዓ.ም ተወልዶ 190 ዓ.ም የሞተው፣ በልጅነቱ የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ከነበረው ከሊቃርጶስ የተማረ እንዲሁም የልዮን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት የነበረው ሔሬኔዎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው የሆነ እንዲሁም ፍጥረቱን ለማዳን ሰው የሆነ አምላክ እንደ ሆነ ያምናል::

## ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ

*"በሥላሴ ማመን ይገባሃል?"* የሚለው የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቀለሜንጦስ ኢየሱስ በባሕርይው ከአብ እንደሚያንስ ያምን ነበር ሲል በሚከተለው መልኩ ይሞግታል:—

> በ215 እዘአ አካባቢ የሞተው የእስክንድርያው ክሊመንት እግዚአብሔርን፣ "ያልተፈጠረ፣ የማይሞትና ብቻውን እውነተኛ አምላክ የሆነ" ብሎታል:: ወልድ ደግሞ፣ አንዳች ነገር ከማይሳነው አብ ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ያለው እንጂ ከአብ ጋር እኩል እንዳልሆነ ተናግሯል::

እንደ ሌሎቹም በዚህም ስፍራ አከራካሪ የሆነው ነጥብ ከትእምርተ ጥቅስ ውጪ ያለው ክፍል ነው::

የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ይህን ይበል እንጂ፣ ቀለሜንጦስ ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር በተቃረነ መልኩ እንዲህ ይላል:—

> "ክርስቶስ ኢየሱስ፣ በእውነት የተገለጠ አምላክ፤ ልጁ ከመሆኑ የተነሣም ከዓለማት ፈጣሪ ጋር እኩል የሆነ"[77]:: እንደ አብ አምላክ[78] ነው:: "የአብ ዘላለማዊ ልጅ"[79] ነው:: አብ ከወልድ ጋር ያልነበረበት ጊዜ የለም[80]::
>
> "መለኮታዊ ቃል፣ እርሱ የፍጹም አምላክ መገለጥ ነው፤ እርሱ ከዓለማት ፈጣሪ ጋር እኩል ነው"[81]::
>
> "ቃል ጅማሬ የሌለው ዘላለማዊ ነው፤ ያው ቃል የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ በባሕርይው ዘላለማዊ እንዲሁም ካልተፈጠረው አምላክ ጋር እኩል ነው"[82]::

---

[75] ሐዋርያው ዮሐንስ አየሱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን የተናገረባቸውን ምንባባት በቀጣዮቹ ምዕራፎች ላይ በስፋት ለማየት እንሞክራለን::
[76] *Against Heresies,* Book I, ch. 8, section 5(11 ).
[77] Clement of Alexandria, *Exhortation to the Heathen* 10, in *ANF,* 2:202.
[78] Clement, *The Instructyor* 1.8, 1.11, in AnF, 2:227, 234.
[79] Clement, *Exhortation to the Heathen* 12, in ANF, 2:206.
[80] Clement, *Miscellanies [Stromata]* 5.1, in ANF, 2:444.
[81] Clement, *Exhortation to the Heathen,* ch. 10.

## ጠርጡልያኖስ

ጠርጡልያኖስ ለሥላሴ አስተምህሮ የምንገለገልባቸውን ሙያዊ ቃላት (ለምሳሌ "ሥላሴ"፣ "ሦስት አካላት"፣ "አንድ አምላክ") የቀመረ የቤተ ክርስቲያን አባት ሆኖ ሳለ፣ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጠርጡልያኖስ በአስተምህሮተ ሥላሴ የማያምን እንዲያውም አረዮሳዊ አስተምህሮ የነበረው ሰው ነበር የሚለው ትምህርቱ ሲበዛ የሚያስደንቅ ነው።

ጠርጡልያኖስ በግልጥ፣ "ትምህርተ ሥላሴ ማለት አንድ አምላክ ሦስት አካላት—አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው" ሲል የጻፈ ቢሆንም የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ ግን፦—

> ብ230 እዘአ አካባቢ የሞተው ተርቱልያን እግዚአብሔር የሁሉም የበላይ መሆኑን አስተምሯል። እንደሚከተለው ብሎ ነበር አብ ከወልድ የተለየና የበለጠ ነው። ወላጅ ከልጁ፣ ላኪም ከተላኪው የተለየ እንደ ሆነ የታወቀ ነውና፤ በተጨማሪም ወልድ ያልነበረበት ጊዜ ነበር...ማንኛውም ነገር ከመገኘቱ በፊት እግዚአብሔር ብቻዉን ይኖር ነበር።

ጠርጡልያኖስ አብና ወልድ የተለያዩ አካላት እንደ ነበሩ መቀበሉ እሙን ቢሆንም፣ ወልድ ያልነበረበት ጊዜ ነበረ...ማንኛውም ነገር ከመገኘቱ በፊት እግዚአብሔር ብቻውን ይኖር ነበር የሚለው ገለጻ ከመጠበቂያ ግንብ እንጂ ከተርቱልያኖስ ብርዕ የመነጨ አይደለም።

አስገራሚው ጉዳይ ይኸው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጽሑፍ ከላይ የተጠቀሰውን ጉዳይ ከማለቱ በፊት ጠርቱልያኖስ ሥላሴ የሚለውን ቃል እንደ ተጠቀመ ዘ ካቶሊክ ኢንሳይክሎፒዲያን በመጥቀስ እንዲህ ይላል፦—

> በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ ሦስቱን መለኮታዊ አካላት አጠቃልሎ የሚያመለክት አንድ ቃል እስካሁን ድረስ አልተገኘም። ትራያስ የሚለው የግሪክኛ ቃል በላቲን ትሪኒታስ ተብሎ የተተረጐምው ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ኢየሱስ ከሞተ ከ180 ዓመት በኋላ በአንጾኪያው ቴዎፍሎስ ጽሑፍ ውስጥ ነው...ከዚያም ትንሽ ቆይቶ ወደ ላቲን የተተረጐመው ትሪኒታስ በተርቱልያን ጽሑፍ ውስጥ ሰፍሮ ተገኝቶአል።

አስደናቂው ጉዳይ የድርጅቱ መጽሐፍ አንድ፣ የጵሮቴስታንት ጽሑፍን በመጥቀስ፣ የሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም...እስከ 4ኛው ሞ ዘመን ድረስ ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ትምህርት ውስጥ መደበኛ ቦታ አልተሰጠውም ነበር እያለ መልሶ ዘ ካቶሊክ ኢንሳይክሎፒዲያን በመጥቀስ፣ ትሪኒታስ በተርቱልያን ጽሑፍ ውስጥ ሰፍሮ ተገኝቶአል ማለቱ ድርጅቱ ራሱ በእማኝነት የሚያቀርባቸው ሰነዶች የእርሱን ሐሳብ እንማይደግፉ የሚያሳይ ነው።

### ቅድመ ጉባኤ ኒቂያ አበው ስለ ሥላሴ ምን ይላሉ?

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከውልደቷ ጀምሮ በዚህ ምድር በኖረችባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ ህልውናዋን የሚፈታተኑ በርካታ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች ገጥመዋታል። በአንጻራዊነት

---

[82] Fragments, Part I, section III.

ሲታይ፣ አንዳንዶቹ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ሲያገኙ፣ አንዳንዶቹ ግን በየትኛውም የታሪክ ዘመን ሳያጨቃጭቁ ያለፉበት ጊዜ የለም ማለት ይቻላል:: ከእነዚህ የነገረ መለኮት ጥያቄዎች ውስጥ ትምህርተ ሥላሴ ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል ቢባል እብለት አይሆንም:: በየዘመናቱ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ የተረዱት አስተምህሮ ነውና::

የትምህርተ ሥላሴ ቀዳማይ አመንጪ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም፣ በሐዋርያት እግር ሥር የተማሩ ቀደምትም ሆኑ ደኀርት[83] የቤተ ክርስቲያን አበው ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ ምን አሉ የሚለውን ጉዳይ መቃኘት፣ የተዛባ የታሪክ መረጃ ያላቸውን ሰዎች ለማቅናት ጠቀሜታ ስላለው፣ ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን በእማኝነት እናቀርባለን::

ትምህርተ ሥላሴን እንደ አርዮስ ካሉ የመናፍቃን ጥቃት በመጠበቁ ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ የነበረው አትናቴዎስ (Athanasius) ቢሆንም፣ ርእሰ ጉዳዩን በጠለለና በዳበረ መልኩ ያቀረቡት ቀጰዶቃውያን አበው[84] ናቸው::

በርካታ ሰዎች በተለይ መናፍቃን፣ ትምህርተ ሥላሴ ከቃለ እግዚአብሔር የተቀዳ ሳይሆን፣ ከጉባኤ ኒቂያ በኋላ[85] የመጣ ባዕድ አስተምህሮ ነው የሚል አመለካከት አላቸው:: ጉባኤ ኒቂያ በሮማው ቄሳር ቈስጠንጢኖስ[86] ተጠርቶ፣ የአንድ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበረው አርዮስ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር በሁሉ ነገር ትክክል አይደለም" የሚለውን ትምህርቱን ለመመርመር የተቀመጠ ጉባኤ ነው::

ጉባኤው አርዮስን አውግዞና ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው የሚለውን መሠረተ እምነት አጽንቶ ያለፈ ጉባኤ ቢሆንም፣ አንዳንድ ሰዎች ትምህርተ ሥላሴ ከኒቂያ ጉባኤ በፊት አልነበረም የሚል የተሳሳተ ግንዛቤና ሙግት አላቸው:: ጉባኤ ኒቂያ ብሉያትንና ሐዲሳትን እያጣቀሰ አስተምህሮውን ደርዝ ባለው መልክ ያብራራ ጉባኤ እንጂ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተቀመጠውን ትምህርት ያስተላለፈ ጉባኤ ላለመሆኑ ታሪክን በመጥቀስ እማኝ በማፈላለግ ይህን የተሳሳተ የታሪክ ግንዛቤ፣ የታሪክ እማኝ በማቅረብ ስሕተቱን ማጋለጥ አግባብ ስለሚሆን፣ ከጉባኤ ኒቂያ በፊት የነበሩትን የቤተ ክርስቲያን አበው በርእሰ ጉዳዩ ላይ ምን ብለው ዐለፉ የሚለውን ጉዳይ በአስረጅነት ለማቅረብ እሞክራለሁ:: ይህ ጽሑፍ ዳሰሳዊ ጥናት ስለሆነ፣ የሁሉንም አበው እማኝነትና ትምህርት በስፋት ማቅረብ ስለማይቻል፣ የጥቂቶቹን ብቻ በናሙናነት ቈንጥረን በመውሰድ እናቀርባለን:: ይህን የምናደርገውም የእነዚህን አበው ጽሑፍ በቀጥታ በመተርጐም ነው::

---

[83] ደኀርት ማለት ኋለኛ፣ የኋላ፣ ታናሽ፣ ተከታይ ወዘተ ማለት ነው::

[84] ቀጰዶቃውያን አበው (Cappadocian Fathers) የሚባሉት፣ የቂሳርያው ትልቁ አባት ባስልዮስ (Basil The Great)፣ ጐርጐርዮስ ዘእንዚናዙ (Gregory of Nazianzus) እንዲሁም ጐርጐርዮስ ዘኑሲስ (Gregory Nyssa) ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስም የምንጠቅሰው፣ የጥንት ብራና መጻሕፍት በሚጠቀሙበት መንገድ ነው:: የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዐውዳዊ ነገረ መለኮት (contextualize theology) የሚለውን ጉዳይ ትኩረት የሚሰጡበት እስከ ሆነ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ስያሜ በተመለከተ ትልቅ ትኩረት ሊሰጡበት የሚገባ ይመስለኛል::

[85] ጉባኤ ኒቂያ በጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 325 ዓ.ም በጁሊያን የዘመን አቈጣጠር 318 ዓ.ም የተካሄደ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው::

[86] በወቅቱ የአገረ ሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረ::

**ጶሊቃርጶስ** (Polycarp) በ70 ዓ.ም ተወልዶ በ155 ዓ.ም ወይም ደግሞ 160 ዓ.ም የሞተ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረ እንዲሁም የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው ትምህርተ ሥላሴን በተመለከተ እንዲህ ብሏል:-

- *"ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ሆይ…ዘላለማዊና ሰማያዊ በሆነው ሊቀ ካህናት በምትወደውና ባከበርኸው ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለአንተና ለእርሱም እንዲሁም ለመንፈስ ቅዱስ ለአሁንም ሆነ ለዘላለም ክብር ይሁን"* (n. 14, ed. Funk; PG 5.1040).

**ጠርጡሊያኖስ ወይም ተርቱሊያኖስ** (Tertullian 160-215) አፍሪካዊ ዐቃቤ ክርስትና እንዲሁም የነገረ መለኮት ሊቅ ነው። ክርስትናን ከመናፍቃንና ከሌሎች ሐያስያን ለመከላከል ብዙ ጽፎአል።

- *"አብና ወልድ ሁለት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ደግሞ ሦስት መሆናቸውን እንገልጻለን። የቍጥሩም ቅደም ተከተል ከድኅነት/ድነት አንጻር ነው. . .ይህም አንድነትንና ሦስትነትን መሠረት አድርጎ ሦስቱንም ማዕከል ያደረገ ነው፤ እነርሱም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ። [አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ] ሦስት ናቸው. . .ነገር ግን በባሕርይ ሳይሆን በገጽ፤ በኀይል ሳይሆን ነገር ግን በዐይነት። በባሕርይና* (substance) *በኀይል አንድ ናቸው፤ ምክንያቱም አንድ አምላክ ብቻ ስላለና ይህም ባሕርይ፣ ገጽና ዐይነት በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ዙሪያ ያለ በመሆኑ"* (Adv. Prax. 23; PL 2.156-7፤ *የመጀመሪያውን ቅንፍ አይጨምርም*)

**አርጌንስ** (Origen 185-254) የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁር ነው። አርጌንስ ክርስትናን ከተለዩ ሐያስያን የተከላከለና ክርስትናን በተመለከተ ብዙ የጻፈ ሰው ነው።

- *"የእግዚአብሔር ቃል ወይም የእግዚአብሔር ጥበብ ጅማሬ አለው የሚል ማንኛውም ሰው፣ ቢያንስ እግዚአብሔርን መናቁ እንደ ሆነ ልብ ሊለው ይገባል. . .ምክንያቱም እግዚአብሔር ባለፉት ዓመታትም ሆነ ዘመናት ወይም ከዚህ ውጪ ሊገመት በሚችልበት ጊዜ ሁሉ፣ እግዚአብሔር የጥበብ ባለቤት ነውና . . . ይህ እውነት ለእግዚአብሔር አብ እንደ ሆነው ሁሉ ለወልድም ነው"* (De Princ. 1.2.; PG 11.132)።
- *"እውነታው ይህ ከሆነ [መንፈስ ቅዱስ አሁን እንደ ሆነው ሁሉ ዘላለማዊ ካልሆነ፣ በዘመናት ውስጥ ዕውቀትን ገብይቶ መንፈስ ቅዱስ መሆን ከቻለ] መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ዓለም መንፈስ ቅዱስ መሆን ካልቻለ፣ እንደማይለወጠው አብና እንደ ልጁ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ አንዱ አካል ነው ማለት አይቻልም"*[87]
- *"የመለኮት ምንጭ ብቻ ሁሉን ነገር በቃሉና በምክንዩው የሚይዝ ከሆነ፣ በሥላሴ አካላት ውስጥ መበላለጥ ወይም መተናነስ የለም"*[88]

**ሔሬኔዎስ** (Irenaeus) በ115 ዓ.ም ተወልዶ 190 ዓ.ም የሞተ፣ በልጅነቱ የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ከነበረው ከሊቃርጶስ የተማረ እንዲሁም የልዮን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት የነበረ ሰው ነው:-

- *"ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ እንዲሁም እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ብትበተንም፣ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያትና ከእነርሱ ደቀ መዛሙርት የተቀበለችው የሚከተለውን መሠረተ*

---

[87] Alexander Roberts and James Donaldson, eds., *The Ante-Nicene Fathers,* Grand Rapids: Eerdmans, 1975 rpt., Vol. 4, p. 253, de Principiis, 1.111.4

[88] Roberts and Donaldson, *Ante-Nicene Fathers,* Vol. 4, p. 255, de Principii., I. iii. 7

> እምነት ነው:- ሁሉን ቻይ የሆነና ሰማይንና ምድርን እንዲሁም ባሕርን በእነዚህም ውስጥ የሚኖሩትን ሁሉ የፈጠረ አንድ እግዚአብሔር፤ በእግዚአብሔር ልጅ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ለድነታችን ሲል ትስብእት የሆነ፤ በመንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔርን ዘመን በነቢያቱ ያበሠረ እንዲሁም የተወዳጁ ጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት፣ ከድንግል መወለድ፣ ሕማም፣ ከሙታን መነሣት፣ በአካለ ሥጋ ወደ ሰማይ ማረግ፣ 'ሁሉን አንድ አድርጎ ለመሰብሰብ' በአብ ክብር ከሰማይ መገለጥ፣ የሰው ልጆችን ሁሉ በአዲስ አካል ከሙታን ማስነሣት፣ ይኸውም ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታችንና አምላካችን እንዲሁም አዳኛችንና ንጉሣችን መሆኑን፣ በማይታየው አብ ፈቃድ 'በሰማይና በምድር ከምድርም በታች' ያለ ጉልበት ሁሉ እንዲንበረከክለት፣ ምላስም ሁሉ ለሁሉ ኀጢአት ብሎ እንደ ተሰዋ እንዲመሰክርለት ነው. . ." (Against Heresies X.l)፡፡ p

ከጉባኤ ኒቂያ በፊት የነበሩት እነዚህ የእምነት አባቶች እንዲህ ዐይነት እምነት ያላቸው ከሆነ፣ የአስተምህሮው ቀዳማይ አመንጪ ጉባኤ ኒቂያ ሳይሆን ቃለ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው፡፡ የሥላሴ አስተምህሮ ጠንሳሽ የኒቅያ ጉባኤ ቢሆን ኖሮ፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ከቀድሞው አስተምህሮ ጋር የማይጣጣም ነው በሚል ተቃውሞውን ለምን አላቀረበም? እንዲህ ዐይነቱ ተቃውሞስ በታሪክ ለምን አልተዘገበም?